# ተደብቆ የቆየው ሌላው የኢህአፓ ታሪክ ገጽታ

በአሰፋ ነጋሽ - ታህሳስ 2006 ዓ. ም. አምስተልፌን (ሆላንድ)



ብርሃነመስቀል ረዳ



ጌታቸው ማሩ

ባለፉት አርባ ዓመታት አብዮት የሚባል ሰፊ የሆነ ስር-ነቀል ማህበራዊ እንቅስቃሴ መጥቶ የኢትዮጵያን ገጽታ ባልታሰበ ሁኔታ ቀይሮአል። በእርግጥ አብዩቱ አንዳንድ በጎ ለውጦችን ማስከተሉን አይካድም (የሃይማኖት እኩልነት መረጋገጥ ወዘተ)። የኢትዮጵያ አብዮት የኢትዮጵያን ነባር ችግሮች ይፈታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ቢሆንም ቅሉ የኢትዮጵያን ነባር ችግሮች ይበልጥ ውስብስብ ከማድረግም አልፎ አዳዲስ ችግሮችን ወልዶልናል። በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ በመሪነትም ሆነ በጀሌነት ተዋናይ የነበረው **ያ ትውልድ** የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ አብዮት እያለ ማህበረሰባዊ ማእበል ውስጥ በስሜታዊነት ከመቀላቀሉ ባሻገር ያ የገባበት አብዮት እራሱንም ሆነ ሀገሪቱን ኢትዮጵያን ወዴት እንደደሚያደርሳት፤ ምን ውስጥ ሊከታት እንደሚችል፤ ይህ አብዮት በሀገሪቱ ላይ ከሩቅ (የምእራቡና የምስራቁ ዓለም ፍትጊያ) እና ከቅርብ መንግስታት (የጎረቤት መንግስታትና በቀይ ባህር አካባቢ ያሉ የአረብ ሀገሮች) የሚያመጣውን ጣልቃገብነትና በሀገሪቱም ላይ የሚያከትለውን የቅርብና የሩቅ ጊዜ ጉዳቶች የሚያውቅበት አግባብ አልነበረም። ያ የኢትዮጵያን ህዝብ ህይወት በበጎ መልክ ይቀይራል የተባለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ የዚያን እንቅስቃሴ መሪዎችና ተዋናዮች በተለይም ትኩስ የህብረተሰብ አካል የሆነውን የኢትዮጵያን ወጣት ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎታል። የኢትዮጵያ አብዮት ቤተሰብን በትኖአል፤ ልጆችን ያለ አሳዳጊ፤ ወላጆችን ያለጠዋሪና ቀባሪ፤ቀዬዎችን ያለ አባወራዎችና ወጣቶች አስቀርቶአል። አብዮት በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ በጎ ባህላዊ እሴቶችን አጥፍቶአል (በህግ አምላክ የመሳሰሉት ዘመን ተሻጋሪ የነበሩ ጥልቅ የህግ አፍቃሪነታችን መገለጫዎች ጠፍተው በእነሱ ምትክ አብዮት ከምንም ነገር በላይ ናት፤ አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚሉ ብሂሎች ነገሱ)። በዚህ

ዓይነት የሰውን ልጆች ነጻ አወጣለሁ ያለው አብዮት የነጻነት መሰረትና መገለጫ የሆነውን ሰብዓዊነት ከማህበረሰባችን ባህል ውስጥ ጭራሹኑ አጠፋው። አብዮት የማህበረሰባችንንም ባህልና አመለካከት ይበልጥ ኢሰብዓዊ በማድረግ በእድሜ የገፉ አዋቂዎች በህግ አምላክ እያሉ ኃይለኛን የሚከላከሉበትን፤ በእድሜ ህጻናት ተማሪዎች በነበርንበት ጊዜ በየኔታ፤ በዳዊታቸው እያልን ጠበኞችንና ኃይለኞችን ስንከላከልባቸው የነበሩትን ዘመን ተሻጋሪ የህሊና ዳኝነትን የተላበሱ የሃይማኖት፤ የሞራልና የህግ እሴቶቻችንን አሽቀንጥሮ ጣላቸው። በዚህ ዓይነት የሚከተሉትን ዓይነቶች የሰውን ልጅ ሰብዕና ዝቅ የሚያደርጉ፤ ለህሊና የሚሰቀጥጡ ስንኞች የኢትዮጵያ ህጻናት የሚያዜሟቸው አዝማቾች ሆኑ። በዚህም ኢትዮጵያዊ ሰብዕናችን ሟሸሸ።

*እሰይ እሰይ ደስ ማለቱ እሰይ እሰይ ደስ ማለቱ*
*አናርኪስት ምንደኛ ከመንገድ ላይ ተዘርሮ ማየቱ*
*ያ ምንደኛ የኢህአፓ ቅጥረኛ*
*ከመንገድ ላይ ተዘርሮ ሲተኛ።*

እያሉ ታዳጊ ህጻናት እንደ በጎ ነገር ይህንን ህሊና-አዋኪ የሆነ መዝሙር በደርግ ካድሬዎች አማካይነት ኢትዮጵያ ምድር ላይ እንዲዘምሩ ተደረገ። ከፍተኛ ሃያ ሶስት ስር በሚገኘው የቀበሌ 08 እስር ቤት ውስጥ የኢህአፓ ታዳጊ ወጣቶች አባል በመሆኑ ታስሮ የነበረ አንድ ዛሬ በአሜሪካን ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወዳጄ እሱ በታሰረበት በዚህ የቀበሌ እስር ቤት ውስጥ ከእሱ በእድሜ ከፍ ያሉ ወጣቶች ለግድያ ወደ ውጭ ከመወሰዳቸው በፊት እሱና እሱን የመሰሉ ታዳጊ ህጻናት ተነስተው ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን መዝሙር እንዲዘምሩ ይገደዱ እንደነበረ በሃዘን ገልጾልኛል። በተቃራኒው የደርግ መንግስት ተቃዋሚዎች የምንባለውም የኢህአፓ ተከታዮች እንደዚሁ "ፋሽስትና ባንዳ ስለምንላቸው የደርግ ተከታዮች ተመሳሳይ ኢሰብዓዊንተን የተላበሱ ስንኞችን መቋጠር ጀመርን። ያኔ ህሊናችንን አሽቀንጥረን እንድንጥል በሚያደርግ የግራ ፍልስፍና ድባብ ስር ሆነን እንደ ሰው የሚገልጸንን የህሊና ዳኝነትና የፍትህ አስተሳሰብ በመተው ወደ ኢሰብአዊነት ደረጃ ስለዘቀጥን የምናደርገውን አላወቅንም ነበር። አረ ጃል ተው የሚል የሞራል ስልጣን ያለውም ተቋም ጠፍቶ ቀለም-ቀመስ የነበረውን የኢትዮጵያን ህብረተሰብ አካል እብደት ውስጥ የከተተ ሂደት ውስጥ ገባን። በዚህ ዓይነት አብዮት የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በማይታወቅ መልክ ቀይሮ አለፈ። ማህበረሰባችን ድቅድቅ ጭለማ ውስጥ ገባ። አብዮት የፖለቲካ ባህላችንን ከምንጊዜውም በበለጠ ሰው-በላ (በላዔ-ሰብዕ) አድርጎታል። በማህበረሰባችንም ስነልቡና ላይ የእርስበርስ ጥርጣሬንና መፈራራትን አሳድሮና ተክሎ አልፏል። ማህበራዊ ግኑኝነታችን በከፍተኛ ጥንቃቄና ጥርጣሬ የታጀበ እንዲሆን አድርጎአል። የደርግን መውደቅ ተከትሎ የመጣው የወያኔ አገዛዝ ደግሞ በትንሹ የቀረችንንም ኢትዮጵያዊ ሰብእና ጭራሹን አጥፍቶብን ትላንት በአብዮት ዘመን ሰብዓዊ እሴቶቻችንን ጥለን በመደብ ሚዛን መለካት የጀመርነውን የሰውን ልጅ ሰብዓዊ ዋጋ ዛሬ ደግሞ በዘመነ ወያኔ በጎሳ ማንነት ሚዛን መለካት ጀመርን። በዚህ ዓይነት ትላንት አንድ የኢህአፓ ደጋፊ ሲገደል አናርኪስት ሞተ እንኳን ሞተ፤ አንድ የደርግ ደጋፊ ሲሞት ባንዳ ሞተ የታባቱ እንኳን ሞተ፤ አንድ የቀድሞ የአጼ ሃይለስላሴ መንግስት ባለስልጣን ሲገደል እንኳን ሞተ ይህ አድሃሪ እያልን እንድንል ያደረገን የግራ ርዕዮተአለም እብደት ዛሬ ደግሞ አንድ አማራ ሲሞት ይበለው አንድ ነፍጠኛ ሞተ፤ አንድ ኦሮሞ ሲሞት ይበለው አንድ ኦነግ ሞተ፤ ወዘተ ወደሚል ሰብዓዊ ፍጡራን መሆናችንን ወደሚያስረሳን ደረጃ አድርሶናል። የሰሞኑም የኦነግ ተከታዮች በኖርዌይ ዋና ከተማ ኦስሎ ተሰልፈው በሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት ተሰልፈው ያደረጉት **"እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለንም፤ እኛ ወንጀለኞች አይደለንም፤ እኛ ኦሮሞዎች ነን አታጥቁን"** እያሉ ያደረጉት ጩኸት ይህንን እየጠፋ ያለውን እንደ ሰው፤ እንደማህበረሰብ ሊገልጸን ይገባው የነበረውን ሰብዓዊ እሴታችንን መጥፋትና መመናመን ያሳያል። ባጭሩ ባለፉት አርባ ዓመታት ኢትዮጵያውያን እንደ ሰው የሚገልጹንን በርካታ እሴቶች ሳናውቀው እንደ ቀልድ አጥተናል።

ኢትዮጵያን በተመለከተ እስካሁንም ድረስ ያ አብዮት የተባለው እንቅስቃሴ የለኮሰው እሳት ፍም ሳይጠፋ ማህበረሰባችንን በግራ ፖለቲካ አዋላጅነት በብሄር-ብሄረሰቦች መብት ስም የተጸነሰው የጎሳ ማንነት እሳት ውስጥ እንድትለበለብ በመደረግ ላይ ነች። ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል እንደሚባለው

በአብዮቱ ምክንያት ሀገራችንና የአፍሪቃ ቀንድ የሚባለው አካባቢ የቀዝቃዛው ጦርነት (የምእራቡና የምስራቁ ዓለም) መፋለሚያ ቀጠና ሆኖ ካለ እዳቸው በዚያ አካባቢ ያሉት የኢትዮጵያ፤ የሶማሊያና ዛሬ በአዲስ ሀገርነት የምትታወቀው ኤርትራ ህዝቦች የቀዝቃዛው ጦርነት ዋነኛ እዳ ከፋዮች በመሆን ከፍተኛ የህይወት ዋጋን ከፍለዋል(ትላንት በጦርነትና በረሃብ)። ይህ አልበቃ ብሎ ዛሬ ደግሞ ከቀዝቃዝው ጦርነት ማብቃት በኋላ እንኩዋን የእኛ አበሳና ፍዳ አላበቃም። በወያኔ መንግስት ፊታውራሪነት የሚመራው የኢትዮጵያ መንግስት የአንድን አናሳ ጎሳ አገዛዝ ከመሰረተ በኋላ ስልጣን ማማ ላይ ለዘላለም ለመቆየት የሚያስችለውን ድጋፍ ያስገኝልኛል ብሎ በተማመነበት የጸረ-እስልምና አሸባሪዎች ጎራ ተሰልፎ የፈጸመው ሱማሌን የማተራመስ ድርጊቱ ገና ከወያኔም ስርዓት ማክተም በኋላ ለብዙ የኢትዮጵያ ትውልዶች የሚተርፍ ጥላቻን የሚያቆይልን ነው። እንደ ትግሬ ብሄረተኛነት ሁሉ ለኢትዮጵያዊነት ባለው ስር የሰደደ ጥላቻ የሚታወቀው የኤርትራ ብሄረተኛነት የፈጠራት አዲሲቷ ሀገር ኤርትራ ምድራዊ ሲኦል ሆናለች። ትላንትና ቁጤማና የማሽላ ቆሎ በየአደባባዩ እየበተነ በእልልታ ሻቢያን የተቀበለው የኤርትራ ህዝብ ከዚህ ሻቢያ ከፈጠራላቸው ሲኦል ለማምለጥ ህይወቱን ለአደጋ እያጋለጠ ወደ ሁሉም የዓለም ማእዘናት እየሸሸ ነው። ትላንት የኤርትራ ብሄረተኞች ቅኝ ገዢያችን ያሏት ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ በቀን እስከ ሃምሳ ኤርትራውያን ስደተኞች የኢትዮጵያንና የአዲሲቷን ኤርትራ ድንበር እያቋረጡ የሚሸሹባት የኤርትራን ስደተኞች የምታስተናግድ ሀገር ሆናለች። ዛሬ የኢትዮጵያ፤ የኤርትራና የሶማሌ ህዝቦች ተወላጆች በስደት በሲናይና በሰሃራ በረሃዎች ቀባሪ ሳይኖራቸው የውሻ ሞት እየሞቱ፤ ኩላሊታቸው እየወጣ እየተነገደበት (CNN November 2011 ስለዚህ ጉዳይ ያስተላለፈውን ዘገባ ይመልከቱ) እንዲሁም እሬሳቸው ባንድ ጉድጓድ እየተነባበረ እየተቀበረ አዲሶቹ ትውልዶች የእነዚህ የአፍሪካ ቀንድ ተወላጆች ደግሞ በተራቸው ተጨማሪ እዳ እየከፈሉ ነው። ይህ አላንስ ብሎ ደግሞ ወያኔዎች ሥልጣን ለማራዘም በመሳሪያነት እንዲያገለግላቸው የቆሰቆሱት አክራሪ የሃይማኖት ማንነት (fundamentalist religious identity) የቀዝቃዛውን ጦርነት በመተካት አዲስ ተፋላሚዎችን ሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ጎትቶ በማምጣት ሀገራችንና ሶማሊያን የጦርነትና የውዝግብ ቀጠና አድርጓል። በዚህም ሳቢያ በምእራቡ ዓለምና በዋሃቢስት እስላማዊ ሃይሎች መካከል በሚደረገው ፍትጊያ የሀገራችንና የሶማሊያ ህዝቦች በጦርነት እሳት ወላፈን እየተገረፉ፤ የዚህን የሁለት ባእድ ኃይሎች ጦርነት በህይወታቸው እየከፈሉ ይገኛሉ።ይህ ሁሉ ሁኔታ በዚያ አካባቢ የበቀሉት ተማሩ የሚባሉ ልሂቃን ከስልጣን ወዳድነታቸውና እና ከጠባብ ብሄረተኛነት አስተሳሰባቸው ባሻገር እንደ ሰብዓዊ ፍጡር ስለ ህዝቦቻቸው ማሰብ እንደማይችሉ የሚያሳይ የዚያ የአፍሪካ ቀንድ ተወላጆች ነን የምንለውን ሁሉ በሃፍረት አንገት የሚያስደፉ ክህስተት ነው።

በ1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን አብዮታዊ ሁኔታ በመምራት የኢትዮጵያን ህዝብ ነባር ችግሮች እንፈታለን በማለት በርካታ የግራ አመለካካት ያላቸው ድርጅቶች በአብዩቱ ወቅት ብቅ ብለው ነበር። ከነዚህ በወቅቱ ብቅ ብለው ከጠፉትና በወቅቱ በተለይ በከተሞች አካባቢ ያሉትን በርካታ ትምህርት-ቀመስ ወጣቶች (የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች) ትኩረት ከሳቡት ድርጅቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው **የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)** የሚባለው ድርጅት ነበር። ኢህአፓ የተመሰረተው በሁለት የግራ አመለካከት በሚያራምዱ በሀገር ቤትና በሀገር ውስጥ በተመሰረቱ ማርክሲስት ቡድኖች ውህደት ነው። አንደኛው ቡድን **የአብዮት** ቡድን ሲሆን በሀገር ቤት ውስጥ ተመስርቶ በተማሪው፤ በመምህራንና በተወሰነ ደረጃ በአንዳንድ ሰራተኞች አካባቢ ተከታዮች ነበሩት። ይህ ቡድን አብዮት የሚባል በራሪ ወረቀት ያሰራጭ ነበር። ሁሉተኛው ከሀገር ውጭ የተመሰረተው **Ethiopian People's Liberation Organization (EPLO)** በሚል ስም የሚታወቀው ቡድን ደግሞ በውጭ ሀገር ይኖሩ ከነበሩና አንዳንዶቹም ቀደም ብለው አይሮፕላን ጠልፈው ከሀገር ከወጡ በኋላ በስደት ይኖሩ በነበሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የተቋቋመ ቡድን ነው። ይህ ቡድን ሀገር ቤት ውስጥ ከገባ በኋላ **ዲሞክራሲያ** የሚባል በራሪ ወረቀት ያሰራጭ ነበር። እነዚህ ሁለት ቡድኖች የኢትዮጵያ አብዮት እንደተጀመረ በየፊናቸው **አብዮትና ዲሞክራሲያ** የሚባሉ ተባራሪ የቅስቀሳ ወረቀቶችን በማሰራጨት የፖለቲካ አቋማቸውን ካስተዋወቁ በኋላ በነሀሴ ወር 1967 ዓ.ም ኢህአፓ በሚል ስም የተደራጀ የህቡዕ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋማቸውን አወጁ።

ኢህአፓ ያሰራጭ በነበረው መልእክት እንደ ቻይና አብዮተኞች ከገጠር የሚነሳ የተራዘመ የትጥቅ ትግል (protracted armed struggle) በማድረግ የደርግን መንግስት እጥላለሁ እያለ ለአባላቱና ለተከታዮቹ ቢያሰረዳም በተግባር ግን የአብዛኛዎቹ የድርጅቱ መሪዎች ዓላማ በአቋራጭ መንገድ በከተሞች ውስጥ ህዝባዊ ነውጥ (urban mass insurrection) በማስነሳት ስልጣን ላይ ለመቆናጠጥ እንደነበረ ድርጅቱ ውስጥ ቆይተን በህይወት የተረፍን ወገኖች ከዓመታት በኋላ ይህንን ለማወቅ ችለናል። ይህም ድርጅቱ የተከተለው በከተሞች ላይ ያተኮረ የትጥቅ ትግል ምርጫ በድርጅቱ መሪዎች መካከል የሃሳብ ልዩነት አስከትሏል። በወቅቱ ይህንን የድርጅቱን አመራር ለሁለት የከፈለ የትግል ስልትና ከእሱም ጋር ተያይዘው በድርጅቱ አመራር ውስጥ የተከሰተውን ክፍፍል ከጥቂት በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ከነበሩ ግለሰቦች በስተቀር አብዛኞቹ የድርጅቱ አባሎች የነበርነው ሁሉ የምናውቅበት አግባብ አልነበረም። ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ፤ ቀጥሎም በግራ ድርጅቶች ውስጥ ዛሬ ደግሞ ስልጣን ላይ ካለው የወያኔ ትግሬዎች መንግስት እስከ ተቃዋሚ ድርጅቶች ድረስ በዘለቀው የፓለቲካ ባህላችን ምክንያት በአንድ ድርጅት ውስጥ ያሉ አባሎች የተለያዩ አመለካከቶችን ለማስተናገድ የሚያስችል ነጻነት አላገኙም። አንድ ለየት ያለ ሃሳብ ያለው ወገን ሃሳቡን አቅርቦ የሚሰማበት፤ ሃሳቡን ለነጻ ውይይት አቅርቦ የሃሳቡ ፋይዳም ሆነ ጉዳት (merit and demerit) በክርክር ነጥሮ የሚወጣበት አሰራር በፖለቲካ ባህላችን ውስጥ የተለመደ አልነበረም ዛሬም አይደለም። በጊዜው የግራ አመለካካት ባላቸው ድርጅቶች ውስጥ ሰፍኖ ይታይ የነበረው ኢ-ዲሞክራሲያዊ የፓለቲካ ባህል ምክንያት በኢህአፓ አመራር ውስጥ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ የነበሩትን የተለያዩ አመለካከቶች ሊስተናገዱ አልቻሉም። ድርጅቱ ሊከተል የሚገባውን የትግል ስልት አስመልክቶ ከእነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች የሰረጹ የሃሳብ ልዩነቶች ታፍነው ሳይታወቁ ቀርተዋል። በወቅቱ ብዙሃኑ የኢህአፓ አመራር አባሎች የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሁለት የድርጅቱን መሪዎች በአንጀኛነት፤ በድርጅት በታኝነትና አፍራሽነት በመወንጀል ከድርጅቱ አመራር እንዲገለሉና በቁም እስር እንዲቆዩ አድርገዋል። የእነዚህ ሁለት የአመራር አባሎች ሃሳብም ለአባላት እንዳይደርስ፤ አባላት እንዳይወያዩበት ተደርጎና ተደብቆ ሁለቱ አባላት ህይወታቸው አልፎአል። እንደ ሀይማኖታዊ ቀኖና የእውነት መንገድ እኔ ብቻ ነኝ የሚል አስተሳሰብ የሚያራምደው የእነ ሌኒን፤ ስታሊንና ማኦ የግራ አስተሳሰብ የተለየ ሃሳብ ያለውን ወገን በጠላትነት ፈርጆ መምታትና ማስወገድን ያበረታታ ነበር። በዚህም ዓይነት በኢህአፓ ውስጥ የተከሰተው የሃሳብ ልዩነት ታፍኖ ለየት ያለ ሃሳብ ይዘው ብቅ ያሉት ሁለት ግለሰቦችና ተከታዮቻቸው የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው። እነዚህ ሁሉቱን የቀድሞ የኢህአፓ አመራር አባሎች ያኔ በስማቸው ሳይሆን **ጓድ ሀ** **እና ጓድ ለ** በሚል ስያሜ ነበር እንድናውቃቸው የተደረገው። እነዚህ ዛሬ በህይወት የሌሉ በወቅቱ **ጓድ ሀ** **እና ጓድ ለ** በመባል የተሰየሙት የኢህአፓ መሪዎች **አቶ ብርሃነመስቀል ረዳና አቶ ጌታቸው ማሩ** ነበሩ። በቅርቡ በእጃችን የገባውንና አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ በደርግ መንግስት ከሰሜን ሸዋ ተይዞ በታሰረበት ጊዜ ቃሉን የሰጠበትን ሰፊ የሆነ ዘገባ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አንብቦት በጊዜው ስለነበረው ሁኔታ ግንዛቤ እንዲያገኝበት እነሆ ይህ መረጃ በእጃችን የደረሰን ወገኖች ለህዝብ እይታ አቅርበነዋል። በሃሳብ የተለዩት ወገኖች ልዩነቶቻቸው

፩ - በጊዜው ኢህአፓ በከተማ ያካሂድ የነበረውን የከተማ የትጥቅ ትግል አደገኛነትና ጅብደኝነት የተመለከተ፤ ድርጅቱ በከተማ ዐመጽ ስልጣን ለመያዝ ያደረገውን የትግል ስልት ምርጫ የተመለከተ።

፪ - ኢህአፓ በወቅቱ ጠላቶቼ ናቸው በሚላቸው በሃሳብ ከዚህ ድርጅት የተለዩ መኢሶንን በመሳሰሉ ድርጅት መሪዎች ላይ የከፈተውን የግድያ ዘመቻ የሚቃወሙ (የዶክተር ፍቅሬ መርእድንና የአቶ ገብረእግዚአብሄርና ጓደኞቹን ግድያ አጀማመር ይመለከቷል)

፫ - ደርግ ፋሽስት ነው የሚለውን መፈክር ስህተተኛነትና ከሌሎች የፓለቲካ ሃይሎች ጋር አብሮ የመስራትን ሃሳብ የተመለከቱ ነበሩ።

አቶ ጌታቸው ማሩ ከድርጅቱ አመራር እንዲታገድ ከተደረገ በኋላ የኢህአፓ እስረኛ ተደርጎ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ እዚያው አዲስ አበባ ውስጥ ቆየ። በመጨረሻም በአዲስ አበባ ኢህአፓ በደርግ ላይ የከተማ ሽምቅ ውጊያ ለማካሄድ ባደራጀው የትጥቅ ክንፍ አባሎች (armed squad members) በአሰቃቂ

ሁኔታ ተቀጥቅጦ ከተገደለ በኋላ አሬሳው እንኳን ተለይቶ እንዳይታወቅ ፊቱ ላይ ኬሚካል ተነስንሶበት በጆንያ ተጠቅሎ ሽንት ቤት አጠገብ ተጣለ። እኔ አሰፋ ነጋሽ በ1970 ዓ.ም. **ከፍተኛ 25 እስር ቤት** በቆየሁበት ወቅት በአካል ያገኘሁትና በኋላ በደርግ መንግስት የተገደለው የአዲስ አበባ የኢህአፓ የኢንተርዞን የፓርቲ ኮሚቴ ዋና ጸሀፊ የነበረው አቶ ሙህዲን ኡመር (ነፍሱን ይማረውና) ስለዚህ ጉዳይ ጠይቄው የነገረኝ የሚከተለውን ነበር። **"ጌታቸው ማሩ ከብርሃነመስቀል ረዳ ጋር ከድርጅቱ የማእከላዊ ኮሚቴ እንዲገለል ከተደረገ በኋላ ጌታቸው በእስረኛነት ተይዞ በኢህአፓ የከተማ የትጥቅ ክንፍ ታጣቂዎች ጥበቃ ስር ቆየ። ከእለታት አንድ ቀን ጌታቸው ማሩ እሱን ይጠብቁት የነበሩትን ጓዶች እስፖርት እንዲያሰሩት ካስፈቀደ በኋላ ካራቴ ይችል ስለነበረ ጠባቂዎቹን በካራቴ በመምታት ሊያመልጥ ሲል ጠባቂዎቹ ገደሉት"**። በኢህአፓ አመራር አካባቢ ስለ ጌታቸው ማሩ አሟሟት የተነገረው እንደዚህ ያለ ወይንም ይህን መሰል ሀሰተኛ ማስተባበያ እንደሆነ ከዓመታት በኋላ ቆይተን ተረድተናል። የሙህዲን ኡመር አለቃና የበላይ ኃላፊ ሆኖ ትእዛዝ ይሰጥ የነበረውና አሁን በዩጋንዳ በንግድ ስራ የሚተዳደረው **ያ ትውልድ** የተባለው መጽሃፍ ጸሃፊ ክፍሉ ታደሰ ዛሬ በህይወት ካሉት የቀድሞ ኢህአፓ አመራር አባሎች ሁሉ ስለ ጌታቸው ማሩ ግድያ ከማንም በላይ የሚያውቅና ጌታቸው ማሩ በተገደለበት ወቅት እዚያው አዲስ አበባ ውስጥ የነበረ ሰው እንደነበረ ልብ ይሏል። ክፍሉ በጻፈው ያ ትውልድ በሚለው መጽሃፉ ውስጥ የሚከተለውን ነገር ይነግረናል "**By the decision of the EPRP central committee, Getachew had been detained since March 1977. For a period of three months or so, Getchew had been insisting that his case come to a conclusion. The Addis Abeba Interzonal committee (IZ) which had no prison of its own had also been insisting that it was difficult to handle the prisoner. The last action of Getachew Maru precipitated a crisis and the Addis Abeba IZ refused to handle him any more. On this same day, Getachew Maru who overpowered an EPRP guard and tried to escape imperilled his life"** (**The Generation** Part II, page 322). ስለ ጌታቸው ማሩ አሟሟት ክፍሉ ታደሰ ይህንኑ ከላይ የጠቀስኩትን በኢህአፓ አመራር የተሰጠውን ሀሰተኛ ምክንያት በመጽሃፉ ውስጥ አስፍሮአል። እውነቱ ግን ጌታቸው ማሩ በኢህአፓ የአዲስ አበባ የከተማ የትጥቅ ቡድን አባላት በዱላ ተደብድቦ፤ ከተገደለ በኋላ ማንነቱ እንዳይታወቅ ፊቱ ላይ አሲድ ተነስንሶና በጆንያ ተጠቅሎ ተጣለ። ሽመልስ ረታ የተባለው የጌታቸው ማሩ ጓደኛ የጌታቸውን አሰቃቂ ግድያ አስመልክቶ ህይወት ተፈራ ለተባለችው የጌታቸው ማሩ ፍቅረኛ የሚከተለውን እንደነገራት ባለፈው ዓመት ህይወት ተፈራ ባሳተመችው መጽሃፏ ውስጥ በሚከተለው መልክ ጽፋዋለች። "**I heard about his death when I was in prison. I was arrested on June 25. When I was there, I heard that a squad member Surafel Kaba and his colleagues gave a statement during interrogation saying that Getachew was not shot dead. They beat him to death with a club. They put bleach on his face and encased his dismembered body in a sack. The Derg identified him by his ID card and by his thin moustache. I heard that in their interrogation statements, Surafel and Co. stated that, we beat a comrade like Getachew Maru to death. We didn't even have respect to a founding member such as him"** (page 275 of Hiwot Teferra's book entitled **Tower in the Sky"** 2012. ጌታቸው ማሩን እኛ ገደልነው ብሎ ቃሉን ሰጠ የተባለው ሱራፌል ካባ በ1970 ዓ.ም. እኔ ታስሬበት በነበረው ከፍተኛ ሃያ አምስት እስር ቤት ውስጥ አብረን ታስረን የነበረና በኋላ በ1971 ዓ.ም የሞት ፍርድ ተፈርዶበት በደርግ መንግስት የተገደለ የኢህአፓ የከተማ የትጥቅ ቡድን (እስኳድ) አባል ነበር። ክፍሉ ታደሰ ይህንን "አብዮት ልጆቿን ትበላለች" የተባለበትን መራር እውነት ነው ከብዙ አመታት እንኳን በኋላ ለመደበቅ የሞከረው። ዛሬ ደግሞ አብዛኛውን የስደት ህይወቱን በዲሞክራሲያዊ መንግስታት መዲናዎች ያሳለፈው ሌላው የኢህአፓ መሪ ኢያሱ ዓለማየሁ በኩራት አንጃ በሚላቸው ላይ እሱ የሚመራው ፓርቲ የፈጸመውን ትላንት **አብዮታዊ እርምጃ** እየተባለ የተሞካሸውን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሲኩራራበትና እሱ

ከጓዶቹ ጋር ሆኖ ያንን በማድረጉ ኩራት እንደሚሰማው ይነግረናል። ለመሆኑ እነዚህ የኢህአፓ መሪዎች በለስ ቀንቶአቸው ስልጣን ላይ ቢወጡ ኖሮ ማን ይተርፍ ነበር? የሀገራችንስ ፖለቲካ ከስልጣን በፊት ለሰው ልጅ ህይወት ልእልናና ለሰብዓዊነት ቅድሚያ የሚሰጠው መቼ ይሆን? ያንድ የኢትዮጵያ ትውልድ እልቂት ይህንን ካላስተማረን ምንስ ሊያስተምረን ይችላል?

ከቀይ ሽብር/ነጭ ሽብር ዘመን በኋላ የኢትዮጵያን አብዮት በተመለከተ በርካታ መጽሃፍት ተጽፈዋል። በተለይ ኢህአፓን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት 21 ያህል መጽሃፍቶች[1] ታትመዋል (የኢትዮጵያን ተማሪዎች ትግል፤ የግራ እንቅስቃሴና የኢትዮጵያ አብዮትን አስመልክቶ የተጻፉ መጽሃፍትን ለማንበብ ለሚሹ ወገኖች እንዲረዳ በሚል እስካሁን የተጻፉትን መጽሃፍቶች ዝርዝር ከዚህ ጽሁፍ ጋር በግርጌ ማስታወሻነት አቅርቤያለሁኝ)። እነዚህ መጽሃፍት ካንዱ (ከክፍሉ ታደሰ መጽሃፍቶች) በስተቀር አብዛኞቹ የተጻፉት በኢህአፓ ውስጥ በከፍተኛ አመራር ስፍራ ላይ ባልነበሩ አባሎች ነው። እነዚህ መጽሃፍቶች በድርጅቱ አመራር አካባቢ ስለነበሩት መሰረታዊ ችግሮች፤ በወቅቱ የኢትዮጵያን ሁኔታ በተመለከተ በአመራር ላይ በነበሩት አባሎች መካከል የነበሩትን የግንዛቤ ልዩነቶች በስፋትና ጥልቀት አያወሱም። እንደዚሁም እነዚህን የተለያዩ ግንዛቤዎች ተንተርሰው የተነሱ የትግል ስልት ልዩነቶችና አማራጭ ሃሳቦች እንዲታፈኑ በመደረጋቸው ምክንያት በተከሰቱት ችግሮች ላይ ብርሃን-ፈንጣቂ አይደሉም። እስካሁን የተጻፉት ብዙዎቹ መጽሀፍቶች በጊዜው የነበረውን የትግል ውጣ-ውረድ፤ ወከባውን፤ ስቃዩን፤ ርሃቡን፤ ጥማቱን የድርጅቱን አባላት ችግርን የመቋቋም ችሎታ፤ ወኔ፤ የዓላማ ጽናት፤ ጓዳዊ መተሳሰብ፤ መረዳዳት፤ የተከፈለውን መስዋእትነት፤ መካካድ፤ የደርግንና የሱ አጋር የነበሩ የግራ ድርጅቶችን አረመኔያዊነትና ጭካኔ ወዘተ አጉልተው የሚያሳዩ ሆነው አግኝተናቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ድርጅታዊ አምልኮና ጭፍን ታማኝነትን ሳያስቀድሙ ያዩትን ነገር ያሳዘናቸውንም (ለምሳሌ በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን የእርስ በርስ ጥርጣሬ፤ መወነጃጀል ወዘተ) ሆነ በጎ ሆኖ ያገኙትን ሁሉ እንዳዩትና እንደተገነዘቡት ጽፈዋል። ቆመንለታል የሚሉትን የሀገርንና የህዝብን ጥቅም በማስቀደም ሳይሆን በሚያሳዝን መልክ የተወሰኑ የኢህአፓ ካድሬዎችን በመወገን የእነዚህን ካድሬዎች ተክለ-ሰውነት ለመገንባት፤ የሚጠሏቸውን ግለሰቦች ከማኮሰስ ያለፈ ፋይዳ የማይታይባቸው መጽሃፍቶችም ተጽፈዋል። አንዳንዶቹ በመጠኑም ቢሆን በገጠር የተሰማራው (ትግራይና ጎንደር) የኢህአፓ ጦር በሰፈረባቸው አካባቢ ይኖር ስለነበረው የገጠር ህዝብ ህይወትና ጉስቁልና ጽፈዋል። እስካሁን ስለ ኢህአፓ በተጻፉት መጽሃፍት ውስጥ ይህ ሀገርን አድናለሁ፤ ወገንን ነጻነት አጎናጽፋለሁኝ ብሎ የተነሳ ትውልድ ያ የተነሳበት ዓላማ ለምን እንደ ከሸፈ፤ ለነጻነት የቆመ ትውልድ እርስ በርሱ ተናክሶ ለምንና እንዴት እንዳለፈ ወደኋላ ተመልሶ ከሰማእትነትነትና የኢትዮጵያን መስቀል ትውልዳችን ተሸክሞ ነበር ከሚል አጉል ስሜት ባሸገር የዚያን ብዙ ጥፋት አድርሶ የሄደውን የትርምስ ዘመን የሚያሳዩ ብዙ መጽሃፍትን አናይም። **እንደዚሁም እኛ የዚያ ትውልድ አባሎች ዛሬ ኢትዮጵያ ለምትገኝበት አስከፊ ስርዓት መምጣት ባለማወቅ እንዴት አስተዋጽዖ እንዳደረግን የሚያወሱና ከወገንተኛነት ስሜት ባሻገር ሰከን ባለ ሁኔታ አዎንታዊውንና አሉታዊውን የትውልዳችንን አስተዋጽዖች የያዙ አስተሳሰቦች እስካሁን በተጻፉት መጽሃፍቶች ውስጥ ብዙ አናይም።** ይልቁንም ብዙዎቹ ስለ ኢህአፓ የተጻፉት መጽሃፍት ትኩረታቸውን ያሳረፉት “**ያ ትውልድ**” ተብሎ ስለሚታወቀው ባንድ ወቅት በኢትዮጵያ ሀገራዊ የፓለቲካ ሂደት ውስጥ በተለይ በከተሞች አካባቢ ብቅ ብሎ የጠፋውን ያለፈውን ትውልድ የመስዋእትነት ገድል ታላቅነት በመዘከር፤ የአንዳንድ ግለሰቦችን ሰብእናና አስተዋጽዖ በማጉላት ላይ ነው። በኢትዮጵያም ሆነ በስደት የምንኖረው የዚያ ትውልድ ቅሪቶች የሆንን ወገኖች ከፍተኛ የህይወት ዋጋ ከፍለናል፤ በደርግ ስርዓት ውስጥ ከደርግም ሆነ ወያኔን ከመሳሰሉ ድርጅቶች ጋር ባደረግነው ትንንቅ መስዋዕት ሆነናል እያልን የደረሰብንን አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት እንደ ዓይነተኛ **የትውልዳችን ማንነት መገለጫ** ካደረግነው ውለን አድረናል። አስገራሚው ነገር እኛ በህይወት የተረፍነው የቀድሞ የኢህአፓም ሆነ የሌሎች በወቅቱ ተራማጅ የሚባሉ ድርጅቶች አባላት (**መኢሶን፤ ማሊሬድ፤ ኢጭአት፤ ወዝሊግ፤ ሰደድ፤ ኢሰፓ፤ ወዘተ**) ያ የተሳተፍንበትና ብዙዎቻችን የምንኮራበት አብዮታዊ ገድል ያንን የተነሳንበትን **የኢትዮጵያን ህዝብ ነጻነትና እኩልነት** አመጣ ወይ? ብለን ለመጠየቅ አልደፈርንም። **የትግላችንንና የጥረታችን መለኪያ ሊሆን የሚገባው ያ የተነሳንበት የህዝባችን የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄ መመለስ ነው ወይስ እኛ የምንኮራበትና የምንኮፈስበት “መስዋእትነት፤ እስር፤ መገረፍ፤ መቁሰል፤ መሞትና መሰደድ ነው”?** ይህንን አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ ለደርግ ጽህፈት ቤት መርማሪዎች የሰጠውን

ቃል ስናነብ እነዚህን ነገሮች በአንክሮ እንድናስብ እጠይቃለሁኝ። **አቶ ብርሃነ መስቀል ረዳና አቶ ጌታቸው ማሩ በዚያ ድቅድቅ የጨለማ ወቅት ቢያንስ የህይወትን መስዋእትነት ያስከፈላቸውን አማራጭ ሃሳብ በማቀርባቸው ሊመሰገኑ ይገባል።** የዛሬ ሰላሳ ስምንት ዓመት በፊት በኢህአፓ አመራር ውስጥ የተከሰተው የተለያዩ ሃሳቦችን ያለማስተናገድ አባዜ ትምህርት ሳንወስድበት ዛሬ ድረስ በወያኔ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥም መቀጠሉ ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳን ለመማር አለመቻላችንን የሚያመለክት ነው። **በአንድ ድርጅት ውስጥ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ወገኖች በአንጃነት፤ በሰርጎ-ገብነት፤ በአፍራሽነት የማየት ባህል በፖለቲካ ድርጅቶቻችን ውስጥ የጎላና ስር የሰደደ ችግር እንደሆነ የሚያሳየን ዛሬ እንኳን ከገዢው የወያኔ ትግሬዎች ድርጅት ህወሃት ጀምሮ፤ ተቃዋሚ ድርጅቶች እስከተባሉት የመድህን፤ የቅንጅት፤ የመኢሃድ፤ የአንድነት፤ ግንቦት ሰባት፤ ኦነግ ወዘተ የፓለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚከሰቱ የሃሳብ ልዩነቶች ጤናማ ውይይትና ክርክር የማይደረግባቸው መሆናቸውና ወደ መከፋፈልና በጠላትነት ወደ መወነጃጀል ሂደት የሚያመሩ መሆናቸው ነው። ይህን ኋላ-ቀርና የተለያዩ ሃሳቦችን ሊያስተናግድ የማይችል የፖለቲካ ባህላችንን ሳጤን ያ በትውልዳችን ተከፈለ የተባለው የ የህይወት መስዋእትነት ከንቱ እንደነበረ ይሰማኛል።** እነ አቶ ብርሃነ መስቀል፤ እነ አቶ ጌታቸው ማሩ እና ብዙ ስማቸው የማይታወቁ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ህይወታቸውን ያጡበት የነጻነት ትግል ዛሬም እንኳን ማስተማሪያ እንዳልሆነን ስንመለከት ያሳዝነኛል። እነሆ የሃሳብ ልዩነትን ለማስተናገድ አለመቻል ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን ሊያሳይ ይችላል ብዬ በማመን የኢህአፓ መሪዎች ከነበሩት አንዱ ግለሰብ አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ በወቅቱ ለበርካታ የኢህአፓ አባላት ለማድረስ የፈለገውንና የታፈነበትን ሃሳብ (ይህ ሃሳብ የአቶ ጌታቸው ማሩም ሃሳብ ነው) እንድትካፈሉና በዚያውም የተለያዩ አመለካከቶችን ላለማስተናገድ አሻፈረኝ ያለውን የፖለቲካ ባህላችንን ጎጂነት እንድታጤኑ እጋብዛለሁኝ። ወደፊትም እንደዚህ ዓይነት በስቃይ የታጀበ የወል ታሪካችን ገጽታዎች የሚያሳዩ መረጃዎች በእጄ ከገቡ የኢትዮጵያ ህዝብ የማወቅ መብት ስላለው ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ አደርጋለሁኝ። ይህንን የማደርገው ማንንም ግለሰብ ወይም የፖለቲካ ቡድን ለመጉዳት ስል አይደለም። በዚህ አጋጣሚ ዛሬ በወያኔ መንግስት እጅ የሚገኙትን እነዚህን መሰል መረጃዎች የሰበሰባችሁ ግለሰቦችም ሆነ ቡድኖች (እነዚህን መረጃዎች ከወያኔ መንግስት ያገኙ በስደት ከሚኖሩት ወገኖች ውስጥ አሉ) የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን መረጃዎች የማግኘት መብት ስላለው እነዚህን መረጃዎች ገደብ ሳታበጁባቸው ለህዝብ እንድታካፍሉ አሳስባለሁኝ። የእነዚህ ዓይነት መረጃዎች በስፋት መሰራጨት ከትምህርታዊነታቸው ባሻገር ባሳለፍነው የወል ታሪካችን ላይ ወደፊት ጥናት ለሚያደርጉ ኢትዮጵያውያንም ሆነ የውጭ ሰዎች በመረጃ ምንጭነትና በማመሳከሪያነት ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይህን መሰል መረጃዎች የዚያ ዘመን ተራፊዎች(survivors) ሆነው ታሪካቸውን ለመጻፍ ለሚያስቡ ደግሞ ተጨማሪ ማበረታቻና ማስታወሻ ይሆናሉ፤ ስለ ቅርብ ዘመን የወል ታሪካችን የሚጻፏቸውንም ጽሁፎች ይበልጥ የተሟሉና ሚዛናዊ ያደርጋሉ ብለን እናምናለን። አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ ደግሞ ከድርጅቱ ሸሽቶ ከአዲስ አበባ ከወጣ በኋላ በደርግ እስከተያዘበትና እስከተገደለበት ቀን ድረስ ያጋጠመውን ሁሉ በራሱ አንደበት ከተናገረውና በደርግ መርማሪዎች ከተጠናቀረው ቃሉ ትረዳላችሁ።

በህይወት የተረፉት የግራው ትውልድ አባሎች ዛሬም እንኳን ምን ያህል እንደ ሰው ቆም ብለው ሀገራችን ያለፈችበት የጥፋትና የስቃይ ዘመን ለማየት እንዳልቻሉና ዛሬም በዚያው ከጥላቻ አስተሳሰባቸው ውስጥ ዘቅጠው እንደቀሩ ዛሬ በስም እንጂ በተግባር በኢትዮጵያ የፓለቲካ ህይወት ውስጥ የማይታወቀው የኢህአፓ ድርጅት መሪ አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ **“እስቲ የምናውቀው እንጻፍ፤ የኢህአፓ ረጅም ትግል”** በሚል ርእስ የሚከተለውን አሳዛኝም አስገራሚም ነገር ጽፏል።
**“ድርጅቱ ከተመሰረተና ትግሉን ማፋፋም ሲይዝ ሌላው ችግሩ ቀይ ሽብር የተባለው አረመኔ ጭፍጨፋ ነበር። ይህን ግፍ ደጋፊና አጋዥ ሆነው የመጡት የብርሃነመስቀል አንጃዎች ደግሞ ሌላ ድርጅቱ ላይ የመጡበት አጥፊ አንበጣዎች ነበሩ። የእነ ብርሃነመስቀል ጌታቸው ማሩ አንጃ ድርጅቱን ይህ ነው በማይባል ደረጃ ቢጎዳም ድርጅቱ ይህንንም ተቋቁሞ ትግሉን ለመቀጠል መቻሉ ትልቅ ድል ሆኖ ይገኛል። ቀጣይ አንጃዎችም እስከዛሬም ቢሆን የመጀመሪያውን ጎዳናና ጫጫታ ተከትለው ድርጅቱን ሊጎዱና ሊያጠፉ ቢጥሩም ድርጅቱ ተቋቁሞአቸው ህልውናውን ጠብቆ አለ። በዚህ ሁሉ ትግል ተሳትፌ አንጃን ወያኔ እንደሚለው በማምከን ወይም እኛ እንደምንለው ከጥቅም ውጪ በማድረግ ከጓዶች ጋር ሆኜ በመሳተፌ ደስታ ይሰማኛል። አንጃኝነት ብተና ክህደት ወዘተ አገዛዞች ካደረሱብን**

**ጉዳት ያላነሰ ጥቃት አድርሰውብናል። ግን እነሱ ከሰሙ እንጂ ድርጅታችን ከቁስሉ አገግሞ አለና እንዳለ ነው። ለምንና እንዴት ስንል ደግሞ የአባላቱን ጽናትና የመስመሩን ትክክለኛነት የሚጠቁም ነው። ይህ ደግሞ የተወሰኑ መሪዎች ስራ ሳይሆን መላ አባላቱ ህዝባዊ ቃል ኪዳኑን አክብሮ መገኘቱን የሚመለከት ነው ብዬ አምናለሁ”.** ይህን ከላይ የጠቀስኩትን ሃሳብ ያሰፈረው ከሰላሳ አምስት ዓመታት በላይ በዚህ በምእራቡ ዓለም መዲናዎች የኖረው ኢያሱ ዓለማየሁ የተባለው የኢህአፓ መሪ ነው። ስለ ዲሞክራሲ ድርጅቴ ሲታገል ኖሮአል የሚለው ኢያሱ ከእነዚህ ረጅም ዓመታት በኋላ እንኳን የተለየ አመለካከትና አማራጭ ሃሳብ ይዘው የተነሱትን ብርሃነመስቀል ረዳንና ጌታቸው ማሩን ከሰውም በታች ዝቅ አድርጎ **በአጥፊ አንበጣ** መስሏቸዋል። ጌታቸው ማሩም ሆነ ብርሃነመስቀል ያቀረቡት ሃሳብ፤ ያነሷቸው ጉዳዮች በተለይ አብዛኞቹ የኢህአፓ መሪዎች አንድን ወጣት ትውልድ ሃላፊነት በጎደለው መንገድ እስከ አፍንጫው ከታጠቀ የደርግ መንግስት ጋር በከተሞች ውስጥ በትጥቅ እንዲፋለም ያደረጉበትን የተሳሰተ መንገድ ትክክል አይደለም ብሎ የሚያስጠነቅቅ ነበር። **እነዚህ ሁለቱ ሰዎች የደረሱበት ግንዛቤ ትክክለኛ ከመሆኑም በቀር ይህንን እውነታ አስቀድመው ማየታቸው የሚያስመሰግናቸው ነው እንጂ የሚያስወግዛቸው አይደለም። የሁለቱ ግለሰቦች ሃሳብ ሰሚ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ በዚያ ትውልድ ላይ የደረሰውን አላስፈላጊ የህይወት መስዋእትነት በእጅጉ የሚቀንስ፤ የዛሬውንም የኢትዮጵያን ገጽታ የሚለውጥ እንደነበር ላሰምርበት እወዳለሁኝ።** ህሊና ላለውና ከስልጣን ባሻገር ለህዝብና ለሀገር ለሚያስብ ሰው ደርግን “**አንድ ሀሙስ የቀረው መንግስት**” ነው ብሎ እጅግ ደካማ አድርጎ በመሳል (ይህ በተደጋጋሚ **ዲሞክራሲያ** በሚባለው የኢህአፓ ልሳን ሲነገር የነበረ አቅምን ያላገናዘበ ባዶ ድንፋታ ነበር) በከተሞች አንድን ትውልድ ለሞትና ለእስራት ለስቃይ ማጋለጥ የሚኮራበት ሳይሆን የሚታፈርበት፤ ይቅርታ የሚጠየቅበት ድርጊት ነው። የኢህአፓ መሪ ኢያሱ ግን ዛሬም ፓሪስ ላይ ቁጭ ብሎ ይህን ከላይ የጠቀስኩትን ዓይነት ሃላፊነት የጎደለው ሃሳብ ሲጽፍ እሱ እታደጋታለሁ የሚላትን ኢትዮጵያን፤ ሊመራው የሚፈልገውን የኢትዮጵያን ህዝብ ስቃይ እንደ ሰው መለስ ብሎ ላንዳፍታም እንኳን ቆም ብሎ ማየት አልቻለም። ኢያሱም ሆነ ተከታዮቹ ምን ያህል ከኢትዮጵያና ከእውነታ በራቀና እራሳቸው በፈጠሩት የቅዠት ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩ ይህ ከላይ የጠቀስኩት የኢያሱ ጽሁፍ ያሳያል። የኢህአፓው መሪ ኢያሱ ከእሱና በርካታ የሱ ጓዶች የተለየ ሃሳብ ይዘው የቀረቡትን የጌታቸው ማሩንና ብርሃነመስቀል ረዳንና የተከታዮቻቸውን (የእነ በክሪ መሃመድን፤ አቢዩ ኤርሳሞን፤ እንድርያስ ሚካኤልን፤ ጌታቸው አሰፋን በርካታ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን) ህይወት የቀጠፈውን የኢህአፓ አምባገነናዊ የጭካኔ ድርጊት ሊጸጸትበት ቀርቶ ድርጊቱ ከተፈጸመ ከሰላሳ ሰባት ዓመታት እንኳን በኋላ “**በዚህ ሁሉ ትግል ተሳትፌ አንጃን ወያኔ እንደሚለው በማምከን ወይም እኛ እንደምንለው ከጥቅም ውጪ በማድረግ ከጓዶች ጋር ሆኜ በመሳተፌ ደስታ ይሰማኛል**” እያለ ይኮራበታል፤ ይፎክርበታል። ኢያሱ ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ አስተሳሰብ ወጥቶ ከእሱ የግል ስሜትና ጠባብ ድርጅታዊ አምልኮው ባሻገር የሀገርንና የወገንን ፍላጎት ያስቀድማል የሚል እምነት የለኝም። ለኢያሱና እሱን በጭፍን ለሚከተሉት ጀሌዎቹ ዲሞክራሲ ማለት ከእነሱ የተለየ ሃሳብ ያለውን ሰው በጠላትነት ፈርጆ ማጥፋትና ህይወቱን መቅጠፍ ነው። ለአርባ ዓመታት ያህል የዲሞክራሲ መዲና በተባሉት የአውሮፓ መዲናዎች ማለትም ሮም (ትላንት)፤ ፓሪስ (ዛሬ) የሚኖረው ኢያሱ ዓለማየሁ ዲሞክራሲ ምን እንደሆነ ሳያውቅ ለረጅም ዓመታት ብኩን ህይወት መምራቱ ያሳዝነኛል። የኢትዮጵያን የፓለቲካ ምህዳርም ምጸት የተሞላበት መድረክ የሚያደርገው ይህን መሰል አስተሳሰብ ያላቸው ወገኖች ዛሬም ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች አማራጭ እንሆናለን ብለው በተቃዋሚነት ጎራ በመሰለፍ የወያኔ ትግሬዎች መንግስት አማራጭ ሆነው ራሳቸውን ማቅረባቸው ነው። **በእኔ እምነት የግራው ፖለቲካ ምች ወይም ግርፋት መቶን የነበርነው ያንድ ትውልድ አባላት ትላንት ዓለምን በነጭና በጥቁር፤ በወዳጅና በጠላት፤ በአጥፊና ጠፊ ጎራዎች ከፍሎ በሚያየው የግራ ፓለቲካ ታውረንና ህሊናችንን ስተን የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ህይወት አጨልመን ነበር። ህብረተሰባችን ብቻ ሳይሆን እኛም የዚህ ጭለማ ሰለባዎች ሆነን ነበር።** የእኔ ትውልድ (አሁን ከ52 -75 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያለነው የኢትዮጵያ የግራው ትውልድ አባሎች ያካትታል) ትላንት የኢትዮጵያን ማህበረሰብ ታሪክና አመጣጥ በውል ባላጤነ የአይምሮ እንጭጭነትና የፖለቲካ ልምድ ማጣት በተጠናወተው ድባብ ስር ሆኖ ብዙ ጥፋት በራሱም ሆነ በኢትዮጵያ ላይ አምጥቶአል። በህይወት ተርፈን ዛሬው ዘመን ላይ የደረስነው የእኔ ትውልድ አባላት ትላንት ያለፍንበትን ወቅትና ሁኔታ በረጋ መንፈስ ወደ ኋላ ዞር ብለን ባለማወቅ የፈጸምነውን የእኛን ትውልድ ስህተት ለማየት ካቃተን እራሳችንን እንደ ሰው ማሰብ ከሚችሉ የሰው ዝርያዎች ተርታ ለማሰለፍ

የሚያስችለን የሞራል ስልጣን ሊኖረን አይገባም እላለሁኝ። ትላንት ባለማወቅና በድንቁርናችን ምክንያት የፈጸምነውን ስህተት ዛሬ ላይ ሆነን ማየት ካስቸገረን፤ የዚያ ትውልድ አባሎች እኛን ከተከተለውና እኛ ያባባስነው የኢትዮጵያ ችግር ሰለባ ከሆነው የዛሬው ትውልድ ጋር የግኙኝነት መረብ ለመዘርጋት፤ የትውልድ ቅብብሎሽ ለማድረግ አንችልም። በዚህ ዓይነት የዛሬው ትውልድ እነዚህ የእኛን እድል ያጨለሙ ናቸው እያለ እንዲወቅሰንና እንዲርቀን እናደርጋለን። ይህ ስሜት የሚፈጥረው በሁለት ትውልዶች መካከል የሚፈጠር ክፍተትና ቅራኔ ሀገራችንና ዜጎቿን በእጅጉ ይጎዳል።

በዚህ አቶ ብርሃነመስቀል ረዳ በሰጠው ቃሉ ውስጥ የተካተተው ታሪክ ውስጥ በመካከለኛው ምስራቅ ወታደራዊ ስልጠና አግኝቶ ወደ ኤርትራ የገባውና በኋላ አሲምባ በተባለው ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ የተቋቋመው የኢህአፓ የትጥቅ ክንፍ ጥንስስ የነበረው ቡድን (ይህ ወታደራዊ ክንፍ የኢትዮያ ህዝብ አብዮታዊ ሰራዊት ወይም **ኢህአሰ** ተብሎ ይታወቅ ነበር) ከአንድ ዓመት በላይ በኤርትራ ውስጥ በሻቢያ ታግቶ ቆይቶ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት በዚህ ኢትዮጵያዊ ቡድን ላይ የኤርትራን በኢትዮጵያ ቅኝ መገዛትና የኤርትራን ነጻነት እንዲያውቅ ጫናና ተጽዕኖ ለማድረግ እንደነበረ እንረዳለን። **ኢትዮጵያ ለምትባለው ሀገርም ሆነ ኢትዮጵያ ለሚባል ህዝብ ጥላቻ ያለው ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ የጣሊያን ቅኝ-አገዛዝ ስሪትና ውላጅ የሆነው ኤርትራዊነት የሚል የባርነት ማንነት ወራሾች የሆኑ ሁሉ (ሻቢያም ሆነ ጀብሃ) ኢትዮጵያ ለሚባል ሀገርና ህዝብ በጎ ነገር እንደማያስቡ ይህ የእነ ብርሃነመስቀል ቡድን ልምድ ታላቅ ትምህርት ሊሆነን ይገባል።** ኤርትራዊነት የሚል የጣሊያን ቅኝ ገዢዎች ፈጥረው የሰጡትን የባርነት ማንነት የተሸከመ የኤርትራ ብሄረተኛ ሁሉ ለኢትዮጵያ በጎ እንደማያስብ ከሃምሳ ዓመታት በላይ የኤርትራ ብሄረተኛነት (Eritrean nationalism) በኢትዮጵያ ላይ የከፈተውን ጦርነት፤ በተለይ ደግሞ ባለፉት አርባ ዓመታት በእነ ኢህአፓ፤በእነ ወያኔ፤ ዛሬ ደግሞ በእነ ኦነግ፤ በእነ ኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባሮች፤ አርበኞች ግንባርና በእነ ግንቦት ሰባት መሳሪያነት እየገፋበት ያለውን ኢትዮጵያን የማዳከምና የማጥፋት ስራ የዚህ ትውልድ አባሎች የሆናችሁ የኢትዮጵያ ዜጋዎች ሁሉ ልብ ልትሉ ይገባል። ወያኔ ከተቋቋመበት ከመጀመሪያዋ እለት ጀምሮ እጅግ ጸረ-ኢትዮያ አመለካከት ይዞ የተነሳ ቡድን ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የወያኔ መንግስት መወገድ ያለበት ቢሆንም ኢትዮጵያን ምንጊዜም በጎሳ ለመከፋፋል አበክሮ ከሚሰራው የኤርትራ መንግስት ድጋፍ ወስደን ወያኔን እንጥላለን ብለው የሚነግሩንን ወገኖች ግን ለአፍታም ጆሮ ልንሰጣቸው አይገባም። አበው እንደሚሉት “**ውሃ ጠማኝ ተብሎ መርዝ አይጠጣም**”፤ ወያኔን ጠላን ብለን ከኤርትራ መንግስት አንወግንም፤ ለምን ቢባል የኤርትራ ማንነት ከኢትዮጵያ ህልውና ጋር በጽኑ የተቃረነ ስለሆነ። ስለዚህም ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳን በመማር፤ ተመልካች ልቦና፤ አስተዋይ አይምሮን አክለን ከጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ባሻገር (beyond political expediency) በወያኔዎችና በእነሱ ዙሪያ በተሰባሰቡት ጎሰኞች እየፈረሰች ያለችውን ኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም፤ የህዝቧን ህልውና እናስቀድም። እንደ ፈረንሳዮቹ vivre la difference (የሃሳብ ልዩነት ይለምልም)፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ እያልኩኝ እሰናበታለሁኝ።

---

1

## I - እስካሁን ድረስ ኢህአፓን በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ መጽሃፍቶች ዝርዝር፡

1 - **ይድረስ ለባለ ታሪኩ** በአቶ ተስፋዬ መኮንን) 1983 ዓ.ም.

2 - **የዳበሳ ጉዞ** በአቶ ፈቃደ ልመንህ 1994 ዓ.ም.

3 - **ከናይሮቢ እስከ ኢዮቤልዩ ቤተመንግስት** በአቶ ሃርቃ ሀሮዬ ኦዳ, 1997 ዓ.ም.

4 - **ከደመላሽ የመቃብር አፋፍ: የእስር ቤቱ ማኒፌስቶ** በዶ/ር ጫንያለው ካሳ, 2000 ዓ.ም.

5 - **የደርግ እስራት ዘመን** (በአቶ ብርሃኑ ሰርጁ), 2000 ዓ.ም.

6 - **የሚያነቡ እግሮች** በአቶ ግርማይ አብርሃ, 2002 ዓ.ም.

7 – **ከደምቢያ ጎንደር እስከ ዋሽንግተን ዲሲ** በአቶ አስማማው ኃይሉ, 2002 ዓ.ም.

8 – **ምርኮኛ** በወይዘሮ ቆንጂት ብርሃን, 2003 ዓ.ም.

9 - **ኢህአሰ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት ቅጽ አንድ** በአቶ አስማማው ኃይሉ, 2003 ዓ.ም.

10 - **የደም ዘመን (ክፍል አንድ)** በአቶ ታክሎ ተሾመ 2003 ዓ.ም.

11 - **ቀለቤቴን ስጧት** በአቶ ቤልጂግ አሊ፣ ግንቦት 2003 ዓ.ም የታተመ

12 – **የደም ዘመን (ክፍል ሁለት)** በአቶ ታክሎ ተሾመ 2005 ዓ.ም.

13 - **የአሲምባ ፍቅር** በአቶ ካህሳይ አብርሃ ብስራት, 2005 ዓ.ም.

## II - Books Written on EPRP in English Language

1 - **Class and Revolution** by Nega Ayele & John Markakis, 1978

2 - **To Kill a Generation** by Babilie Tola, 1989

3 - **The Generation** (Volume 1) (Kiflu Tadesse), 1993

4 - **The Generation** (Volume 2) (Kiflu Tadesse), 1998

5 - **Negotiating a Lion's Share of Freedom – Adventures of An Idealist Caught in Ethiopian Civil War – A Memoir** (Mekonnen Araya), 2010

6 - **Yanki Go Home, The Life of an Ethiopian Revolutionary & the Fall of Assimba, EPRP's Base** by Ayalew Yimam (alias Mukhtar), 2011

7 - **Tower in the Sky** by Hiwot Teferra, 2012

8 - **Were Negari: A Memoir of an Ethiopian Youth in the Turbulent 70's** by Mohamed Yimam, 2013

**III - የግራውን ፓለቲካ በተመለከተ የተጻፉ ሌሎች መጽሃፍት፤ ከመኢሶን አባል እይታ አንጻር**

1 - በአጭር የተቀጨው ረጅም ጉዞ - መኢሶን በኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ውስጥ በአንዳርጋቸው አሰግድ 1992 ዓ.ም.

**IV - Books written on the Ethiopian Students & Ethiopian Left & Ethiopian Revolution**

1 – **The Ethiopian Revolution,** Fred Halliday, 1981

2 - **Ethiopia: An Heretical Revolution** by Rene Lefort, 1983

3 **Haile Selassie's Students: the Social & Intellectual Background to Revolution 1952-1974** by Randi Ronning Balsivik, 1985

4 - **The Ethiopian Revolution 1974-1987: A Transformation from an Aristocratic to a Totalitarian Autocracy** by Andargatchew Tiruneh, 1993

**5 – The Ethiopian Revolution: 1974-1991** by Teferra Haileselassie, 1997

6 - **The Diary of Terror, Ethiopia 1974-1991** by Dawit Shifaw, 2005

**7 - The Quest for Expression: State & the University in Ethiopia Under Three Regimes,** 1952-2005 by Randi Ronning Balsivik, 2007

8 - **Radicalism & Cultural Dislocation** by Messay Kebede, 2009

9 - **Documenting the Ethiopian Student Movement: an Exercise in Oral History** by Bahiru Zewde, 2010

10 – **Ideology and Elite Conflicts: Autopsy of the Ethiopian Revolution**, Messay Kebede 2011